# The TRUTH ACT:

## መብትዎን ይወቁ

ከጥር 1, 2017 ጀምሮ “ትሩዝ አክት” የተባለ አዲስ የካሊፎርኒያ ህግ፣ በማቆያ እና እስር ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ ስደተኞች መሰረታዊ መብቶች እንዳይጣሱ ይከላከላል።

እርስዎ ወይንም የቅርብ ቤተሰብዎት በኢሚግሬሽን እና ካስተምስ ሕግ ኣስከባሪዎች ከፈቃድዎ ዉጪ በእስርቤት ዉስጥ ቃለ-መጠይቅ ከተደረለዎት፣ ወይንም በስሕተት ከ እስር ቤት ወደ ኢሚግሬሽን እና ካስተምስ ሕግ ኣስከባሪዎች ተላልፈው ከተሰጡ፣ እባክዎን በ **1-844-878-7801** ይደውሉልን። መልእክቶቻችሁን ዘውትር እንከታተላለን ።

“ትሩዝ ኣክት” የተባለው ሕግ ፣ የኢሚግሬሽን እና ካስተምስ ሕግ ኣስከባሪዎችን ከከካሊፎርኒያ ለማስወጣት በሚደረገው ሂደት የመጀምሪያ እርምጃ ነው።

ለተጨማሪ ማብራሪያ **www.catruthact.org** ይመልከቱ።

***(Not Intended as Legal Advice)***

## መልስ ያለመመለስ ወይንም ዝም የማለት ሁልግዜ መብት ኣለዎት።

ከሕግ አስከባሪዎች ጋር ወይንም በነሱ ፊት የሚሰጡት ቃል ተመልሶ እርሶን ሊያጠቃ በሚችል መልኩ እንደማስረጃ ሊቀርብ ስለሚችል፤ የኢሚግሬሽንና ዜግነት ሁኔታዎን፣ ወደ አሜሪካ መቼ እና እንዴት እንደመጡ፣ እንዲሁም ከየት ሃገር እንደሆኑ መናገር የለቦትም።

## በኢሚግሬሽን እና ካስተምስ ሕግ ኣስከባሪዎች ለሚቀርብልዎ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ኣይደለሁም የማለት መብት ኣለዎት።

‘‘ትሩዝ አክት” በተባለው ሕግ መሰረት በኢሚግሬሽን እና ካስተምስ ሕግ ኣስከባሪዎች በእስር ቤት ወይንም ማቆያ ቤት ቃለ መጠይቅ ሊደረግልዎ የሚችለው እርሶ ከፈቀዱና ከፈረሙ በሁላ ብቻ ነው። <u>ይህም ማለት ቃለ-መጠይቅ አላደርግም የማለት እና መልስ ያለመመለስ መብት ኣለዎት።</u>

የኢሚግሬሽን እና ካስተምስ ሕግ ኣስከባሪዎች ቃለ-መጠይቅ ሊያደርግልዎ ከሞከሩ መልስ ያለመመለስ መብትዎን መጠቀም ይችላሉ። **በተጨማሪም ጠበቃዎ እንዲቀርብልዎ የመጠየቅ መብት ኣልዎት።** የኢሚግሬሽን ጠበቃ ከሌለዎት በራሶት ወጪ ወይንም በአንድአንድ አካባቢዎች እንደሚደረገው በበጎ ኣድራጊ ድርጅቶች እርዳታ ጠበቃ ማቅረብ ይችላሉ።

## የኢሚግሬሽን እና ካስተምስ ሕግ ኣስከባሪዎች በእስርቤት ወይንም ማቆያ ቤቶች ዉስጥ እርሶን እየፈልጉ መሆኑን የማውቅ መብት ኣልዎት።

በ “ትሩዝ ኣክት” በተሰኘው ሕግ መሰረት የኢሚግሬሽን እና ካስተምስ ሕግ ኣስከባሪዎች በእስርቤት ዉስጥ እንዲቆዩ ወይንም በእስርቤት ቆይታዎ እንዲራዘም የሚጠይቅዉን መረጃ፣ ፖሊስ ወይንም ሸሪፍ ‘ለእርስዎ ግልባጭ ሊሰጥዎ ይገባል።

ፖሊስ ወይንም ሸሪፍ እርስዎ መቼ ከእስር እንደሚወጡ ለኢሚግሬሽን እና ካስተምስ ሕግ ኣስከባሪዎች ሲገልጹ ለርስዎም፣ ለጠበቃዎ፣ ወይንም እርሶ መርጠው በፊርማዎ ላረጋግጡለት ሰው ሊገለጹ ይገባል። ይህ ለእርስዎ የሕግ ጉዳዮን በሚመለከት ተገቢውን ዝግጅት ኣንዲያደርጉ ኣንዲሁም በቂ ግዜ እንዲያገኙ እድል ይሰጥዎታል።

> በኣብዛኛው ያአካባቢ እስርቤቶች፣ ኣንድን ሰው ከኣገር ለማባረር ሲባል ከተወሰነው ግዜ በላይ በእስር ቤት ማቆየት ከሕግ ውጭ ነው። ያካባቢ ጸጥታ ኣስከባሪዎች (እንደ ፖሊስ እና ሸሪፍ የመሳሰሉ) የኢሚግሬሽን እና ካስተምስ ሕግ ኣስከባሪዎች በሰጡት የማቆያ መረጃ ላይ ብቻ ተመርኩዘው፣ ያለ በቂ እና ኣሳማኝ የዳኛ ትእዛዝ በእስር ካቆይዎት፣ በሕግ ሊከሰሱ እና ለእርሶውም ካሳ ሊክፍሉ ሊገደዱ ይችላሉ።